በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

መስከረም ፳፬ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?

*መግቢያ*

- ከዝነኛው ንጉሥ ከቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት በ325 ዓ.ም. በኒቂያ ከተማ በተሰበሰቡት 318 ሊቃውንት ውሳኔ መሠረት ከተወገዘው ከአርዮስ ጀምሮ የመድኃኒታችንን የባሕርይ አምላክነትና ከአብና ከመንፈስቅዱስ ጋር ያለውን እኩልነት የሚክዱ ነበሩ፤ አሁንም አሉ።
- ስለዚህ ቤተ ክርስቲያናችን እግዚአብሔር ለክብሩ ቀናተኛ መሆኑን ከገለጠበት *ዘጸአ 20፡3-6* እና ሌሎችም አንስቶ ያላትን አስተምህሮ አስመልክቶ በተለያየ መንገድ ማስረዳት ይገባናል።
- ኢየሱስ ክርስቶስ - እግዚአብሔር ወልድ ከሦስቱ አካላት አንዱ ሰው እንደሚሆን፣ መከራ እንደሚቀበል፣ በፈቃዱ እንደሚሞትና ሞትንም ድል ነስቶ እንደሚነሣ ነቢያት ትንቢት ተናግረዋል፤ ምስክርነታቸውንም ሰጥተዋል። *ኢሳ 7፡14፣ 9፡6፣ 53፡4-5፣ ዳን 7፡13-14፣ ሚክ 5፡2፣ መዝ 77(78)፡65…*
- እንዲሁም መድኃኒታችን ለፈጣሪ ብቻ መሰጠት ያለበትን መጠሪያ እና መቅረብ ያለበትን አምልኮታዊ ስግደት እንደተቀበለም መጽሐፋችን ይናገራል። *ዮሐ 1፡1፣ የሐዋ 20፡28፣ ሮሜ 9፡5፣ ቀዳ ጢሞ 3፡16፣ ፊል 2፡10፣ ቀዳ ዮሐ 5፡20።*
- ጌታችን ከአምላክ በቀር ሊደረጉ የማይችሉ ድንቅ ተአምራትን ማድረጉና ሁሉን የያዘ የፈጠረ መሆኑም ተገልጾልናል። *ማር 9፡28…።…*

# ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?

**መግቢያ**

- ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹እግዚአብሔርንም የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፡፡›› ***ቀዳ ጢሞ 3፡16፡፡*** በማለት እንደነገረን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የተገለጠ አምላክ እንጂ እግዚአብሔር ነኝ የሚል ተራ ሰው አይደለም፡፡
- እግዚአብሔር በሥጋዊ ዓይናችን ልናየው የማንችለው ሰማይና ምድርን የመላ መንፈስ ነው፡፡ ከኃጢአት ንጹሕ የሆነ የሚታይ ሥጋን ከእመቤታችን ነስቶ የለበሰው (የነሳው) እናየው ዘንድ ነው፡፡ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ‹‹ጸጋ የሞላብሽ ሆይ…›› ***ሉቃ 1፡28*** መሰለቱ ቀድሞም ጸጋ የሞላባት ከኃጢአት የተጠበቀች መሆንዋን የሚያረጋግጥልን ነው፡፡
- ይህም በሬድዮ ወይም በቴሌቪዥን እንደሚሰራጭ ወይም እንደሚተላለፍ ልናየው የማንችለው ሞገድ ነው፡፡ ልናየው የምንችለው በምስል ወይም በድምጽ ውስጥ ሆኖ ሲቀርብ ነው፡፡
- በኤሌክትሪክ ገመዶች ውስጥ የሚተላለፍ የኤሌክትሪክ ኃይል (Current) የሚታየውም በአምፑል ውስጥ ነው፡፡ የኤሌክትሪክ ኃይል መተላለፊያ ቀጥተኛ መስመሩን ብንነካው ሊነዝረን ብሎም ምን እንደነካን ለይተን ሳናየው ለሞትም ሊያበቃን ይችላል፡፡
- ስለዚህ አምላካችን ሥጋ መልበሱ ወይም ሰው መሆኑ እግዚአብሔርን እናየው ዘንድ የሚያስፈልገን የነበረ ሲሆን ከሚከተሉትም መሠረታውያን ነገሮችም ጋር አይጋጭም፡፡

# ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?

1. ከእግዚአብሔር ኃይል

- አምላካችን እግዚአብሔር ሥጋን መልበሱ ወይም ሰው መሆኑ ሁሉን ቻይነቱንና የሚሳነው የሌለ መሆኑን የሚያመለክተን ነው፡፡ እግዚአብሔር መንፈስ ሆኖ ሊኖር ወይም በሰው፣ በእሳት ወይም በድምጽ አምሳል ሊገለጽ የሚቻለው ነው፡፡

2. ከእግዚአብሔር ቅዱስነት

- አንዳንዶች እንደሚያስቡት የአምላካችን ሰው መሆን ቅዱስ ከመሆኑ ጋር ፈጽሞ አይጋጭም ፡፡ አምላካችን እግዚአብሔር በማንኛውም ቦታ ወይም ነገር ላይ፣ በትንሹም በትልቁም፣ ንጹሕ ባልሆነውም ነገርስ እንኳ ሳይቀር እንደሚገለጥ ሥጋን ሊነሳ (ሊለብስ) ይችላል፡፡

3. ከእግዚአብሔር ፍቅር

- እግዚአብሔር ፍቅር ባይሆን በሰማያዊ ክብሩ በሰማየ ሰማያት በልዕልና መኖሩ በቅቶት እኛን በምድር ጥልቅ ውስጥ እንኖር ዘንድ በተወን ነበር፡፡
- ነገር ግን ወደ እኛ ወርዶ ሥጋችንን ለብሶ በክንዶቹ አቅፎ ለዘላለም ከርሱ ጋር እንኖርባት ዘንድ ወደ መንግሥተ ሰማያት መርቶ ከፍ ያደረገን አምላካችን እግዚአብሔር ይመስገን፡፡

# ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?

3. የእግዚአብሔር ፍቅር…

- ከላይ ከሰማይ ሆኖ በሰማያት ሆኜ እጠብቃችኋለሁና ወደ እኔ ኑ ቢለን በኃጢአት በደከመው ሰውነታችን ወደርሱ መውጣት እንዴት ይቻለን ነበር?
- እርሱ ግን ወደ እኛ መጣ እርሱ ወዳለበትም በእጆቹ አቅፎ ወሰደን፡፡

*ቅዱስ አትናቴዎስ ስለ አምላካችን ሰው መሆን ያቀረባቸው ንጽጽሮች*

1. ከንጉሥ አንጻር የቀረበ ንጽጽር

- ይኖርበት ዘንድ ከተማን ለሚመርጥ ንጉሥ ከተማይቱ ዋና ከተማ ከመሆንዋም በላይ ከፍ ያለ ክብር ይሰጣታል፡፡ ለንጉሡ የሚሰጠውም ክብር በቤተመንግሥቱም ሆነ በከተማው ከፍ ያለ ነው፡፡
- የአገሪቱም ዜጎች ስለደህንነታቸውና ጸጥታቸው ቸል ብለው ጠላት ደፍሮ የከተማይቱን ቅጥሮችና ዜጎችንም ቢመታ ንጉሡ ‹‹በገዛ እጃቸው የመጣባቸው›› ነው ብሎ ቸል ይላቸዋል ወይስ ከዜጎቹ በአንዱ የደረሰውን ጥቃት በራሱ እንደደረሰ ነገር ቆጥሮ ዜጎቹን ለመታደግ መንግሥቱንም ለማስጠበቅ ይነሳል?

# ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?

1. ከንጉሥ አንጻር የቀረበ ንጽጽር…

- አምላካችን ሰው በመሆኑ የተደረገውም ይኸው ነው። አምላካችን ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍስዋ ነፍስን ነስቶ ሰው ለመሆን በማኅፀንዋ ሲጸነስ የሰው ዘርን ሁሉ ሊያድን ነው።
- ለእግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ አይሳነውም። እግዚአብሔር ምሉዕ በኩለኄ ነውና።
- የሰው ልጆች በተፈጥሮ ክብራቸው እንዲኖሩ ለወደደው አምላክ ዓላማ ታዛዥ ባለመሆን ሰይጣን እንዲያሸንፍ መፍቀዳቸው እግዚአብሔርን እንዲተወን አላደረገውም፤ ይልቁኑ ያድነን ይዋጋልንና ጠላታችንን ያሸንፍልን ዘንድ እንዲነሳ አደረገው እንጂ!

2. በሠዓሊ አንጻር የቀረበ ንጽጽር

- አንድ ወንድ ልጅ ብቻ ያለውና ልጁም ረጅም መንገድ ይሄድ ዘንድ የተነሳበትን ንጉሥ እናስብ። ንጉሡም አንድ ሠዓሊ ጠርቶ ልጁ በአጠገቡ በማይኖርበት ጊዜ ይመለከተው ዘንድ የልጁን ሥዕል አሳምሮ ይስልለት ዘንድ ጠየቀ።
- ሠዓሊውም ሥዕሉን ሳለለት። ከጥቂት ጊዜም በኋላ በሥዕሉ ላይ ትልቅ ዕቃ ወድቆበት ሥዕሉን ሙሉ ለሙሉ አበላሸው አጠፋው። ታዲያ አባት ምን ማድረግ ይጠበቅበት ይሆን?

# ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?

2. **በሠዓሊ አንጻር የቀረበ ንጽጽር…**

- አባትም ሠዓሊውን ጠርቶ ሥዕሉን ወደ ነበረበት እንዲመልስለት ቢጠይቀው ሠዓሊው ልጁ ተመልሶ እንዲመጣና ሥዕሉን መልሶ የመሳል ዕድል እንዲያመቻችለት አሳሰበ፡፡
- ልጁም ሲመለስ ሠዓሊው የተበላሸውን ሥዕል ቀዳድዶ አዲስ ሥዕል ለመሳል ቢፈልግም አባትየው በአጽንዖት በመቃወም ‹‹የተወደደውን ልጄን መልክ ዘወትር እመለከትበታለሁና የመጀመሪያውን ሥዕል ሳትቀድ ወደነበረበት መልስ፡፡›› ብሎ ጠየቀ፡፡ ሠዓሊውም በተሰጠው የቀድሞ ሸራ ላይ መልሶ የቀድሞውን ሥዕል ሳለ፡፡ ታዲያ ይህ ምን ማለት ነው?
- እግዚአብሔር እኛን በአምሳሉና በአርአያው ፈጥሮናል፡፡ እኛም ያንን መልካችንን ባጠፋንና ባበላሸን ጊዜ ራሱ ወደ ምድር በመምጣት አዲስ ፍጥረት ፈጥሮ የቀድሞውን የሰው ተፈጥሮ ሳያጠፋው ሰውን ወደቀድሞ ክብሩ መልሶታል ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ጥበቡና ፍቅሩ ምን ያህል ድንቅ ነው!

3. **በአገዳ(ወይም መጠጥ በምንስብበት ቱቦ መሰል ዕቃ)ና በግንባታ አስቤስቶስ አንጻር የቀረበ**

- ቅዱስ አትናቴዎስ የሰውን ተፈጥሮ በኃጢአትና በፍርድ በቀላሉ በእሳት በሚቃጠል አገዳ መስሎታል፡፡ ነገር ግን ይህን አገዳ በእሳት በማይቃጠል አስቤስቶስ ብንጠቀልለው በእሳት ከመቃጠል እናድነዋለን፡፡

# ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?

3. በአገዳ(ወይም መጠጥ በምንስብበት ቱቦ መሰል ዕቃ)ና በግንባታ አስቤስቶስ አንጻር የቀረበ…

- በተመሳሳይ መንገድ ሰው በእግዚአብሔር (በኢየሱስ ክርስቶስ) ፈቃድ ሥር ራሱን ቢያኖር እግዚአብሔር (ኢየሱስ ክርስቶስ) ከፍርድ ወይም ከዘላለም እሳት አድኖ ለዘላለማዊ መንግሥት የበቃ ያደርገዋል፡፡
- ታዲያ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው (ሥጋ ለብሶ በምድር በተመላለሰበት) ጊዜ በእውነት እግዚአብሔር እንደሆነ አረጋግጧል? አዎ! ለተራው (ለተፈጥሮአዊው) ሰው ይልቁንም ለነቢያትም የማይቻላቸውን በርካታ ሥራዎች ሠርቷል፡፡ እነዚህም ሥራዎች በእግዚአብሔር ብቻ የሚቻሉና የሚሠሩ ሥራዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህም ሥራዎች ጥቂቶቹ፡-

1. ፍጹም ቅዱስነት

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንም ሊክደው የማይችለውን ፍጹም የሆነውን ቅዱስነቱን አሳይቶናል፡፡ ‹‹ስለ በደል ከእናንተ መካከል የሚከሰኝ ማነው?›› ያለ እርሱ ነው፡፡ ይህን ሲናገርም በሚያስደንቅ ቅዱስነቱ የተነሳ አንደበት ተዘግቷል፣ ምላስም ተሳስሯል፡፡
- ተራ ሰው ስላልነበረ በሰይጣን ያልተሸነፈ እርሱ ብቻ ነው፡፡ *ማቴ 4፡፡*

# ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?

2. **ፍጹም ሥልጣን**

- ጌታችን አምላካችን በፍጥረታት ሁሉ ሕይወት ባላቸው ፍጥረታትም፣ በሐሳቦች፣ በወደፊት፣ በኃጢአትም ላይ ፍጹም ሥልጣን አለው፡፡
- ***በነገሮች ላይ ያለው ሥልጣኑ፡-*** ***ማቴ 14፡13-21*** እንደተገለጸው በሁለት ዓሳና በአምስት እንጀራ ብዙዎችን በመመገቡ፤
- ***በዕፅዋት ላይ ያለው ሥልጣኑ፡-*** ***ማቴ 21፡18-22*** እንደተገለጸው በየበለስን ዛፍ በመርገሙ፤
- ***በእንስሳት ላይ ያለው ሥልጣኑ፡-*** ***ማር 5፡1-20*** በእሪያዎች ላይ ባደረገው፣ ***ሉቃ 5፡1-11*** ደቀመዛሙርቱ ያጡትን ዓሳ አብዝቶ እንዲያጠምዱ በማድረጉ፤
- ***በሰው ላይ ያለው ሥልጣኑ፡-*** በሕመምና በደዌ የተያዙ ብዙ ሕሙማንን በመፈወሱ፣ በሞት ላይ ወለተ ኢያኢሮስን ከሞት በማንሳት ***(ማር 5፡35-43)***፣ በናይን ያገኛትን መበለት ልጅ ከሞት በማንሳት ***(ሉቃ 7፡11-17)***፣ አልዓዛርን ከሞት በማንሳት ***(ዮሐ 11፡1-44)፣*** ራሱም በሥልጣኑ ከሙታን ተለይቶ በመነሳቱ፤
- ***በመናፍስት ላይ ያለው ሥልጣኑ፡-*** መናፍስትን በአንዲት ቃል እንዲወጡ በማዘዙ ***ማር 5፡1-20፣ ማር 9፡25፡፡***
- ***በኃጢአት ላይ ያለው ሥልጣኑ፡-*** ***ማር 2፡6-8፡፡*** ሽባውን ኃጢአትህ ተሰረየችልህ በማለቱ፤

# ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?

2. **ፍጹም ሥልጣን…**

- ***<u>በሐሳቦች ላይ ያለው ሥልጣን፡-</u>*** ***<u>ማር 8፡16-17፣ ማር 2፡6-8፡፡</u>*** እንደተገለጸው ሰዎች ሳይናገሩ ሐሳባቸውን የሚያውቅ በመሆኑ፤ ‹‹ከጻፎችም አንዳንዶቹ በዚያ ተቀምጠው ነበር በልባቸውም፡፡ ይህ ሰው ስለ ምን እንደዚህ ያለ ስድብ ይናገራል? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአት ሊያስተሰርይ ማን ይችላል? ብለው አሰቡ፡፡ ወዲያውም ኢየሱስ በልባቸው እንዲህ እንዳሰቡ በመንፈስ አውቆ እንዲህ አላቸው፡- በልባችሁ ይህን ስለ ምን ታስባላችሁ?››፡፡
- ***<u>ወደፊት በሚሆነው ያለው ሥልጣኑ፡-</u>*** ***<u>ማቴ 24፡1-51</u>*** ስለ ኢየሩሳሌም መውደም፣ ***<u>ማቴ 26፡34፣ ዮሐ 21፡18-19</u>*** ስለ ጴጥሮስ ክህደትና ስለሰማዕትነቱም በተናገራቸው… ተገልጧል

3. **የሚያስደንቅ ሁሉን ቻይነት**

- ጌታችን ልብን ሁሉን ማለፍ በሚችል ኃይሉ ሁሉን አሸንፏል፡፡ ክርስትና በፍጥነት በዓለም የተስፋፋው ከየሥፍራው በመረጣቸው እንደተራ ይቆጠሩ ከነበሩና መንፈስቅዱስን ተቀብለው አልጫውን ዓለም ሊያጣፍጡት በቻሉት ሰዎች ነው፡፡
- በኃጢአት የደነደነውን የሰውን ልቦና ሰብሮ ንስሐ ለመግባት ያበቃው ዘንድ አንድ ወቅት ብቻ በቂው ነው፡፡ ይህም ኃጢአተኛ ተከታታይነት ባለው ሃይማኖታዊ ክትትል ለቅድስና ሊበቃም ይችላል፡፡ ታዲያ ይህንን አስቀድሞ ይህን የተናገርነውን ሁሉ ሰውን የፈጠረው ኋላም ይለውጠው ዘንድ ብቻውን የሚችል እግዚአብሔር ካልሆነ ማን ሊያደርገው ይችላል?
- የተወደዳችሁ ምዕመናን! ፍጹም መድኃኒት፣ የሚያፈቅር አባትና ‹‹መዳንም በርሱ ብቻ የሆነ፡፡›› ***<u>የሐዋ 4፡12</u>*** የተባለ አምላካችንን ፈጽመን አውቀን ፈቃዱን እንፈጽም ዘንድ ፈቃዱ ይሁንልን!

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org